

ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን አነፃ

- ኢየሱስ ሲያስተምር፣ ሲፈውስና ብዙ ተአምራትን ሲያደርግ ቆየ። አይሁዳውያን በየአመቱ የሚያከብሩት የፋሲካ በአልም እየተዳረሰ ነበር። ኢየሱስም በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ ወደኢየሩሳሌም መጣ። ብዙዎች ልብሶቻቸውን በመሬት ላይ አንጥፈውና የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው "ሆሳዕና በአርያም!" እያሉ ይጮኹ ነበር። በእርግጥም የፈንጠዚያና የደስታ ጊዜ ነበር።

- ኢየሱስ ወደ መቅደስ ገባ፤ በዙሪያው ያለውንና እየሆነ የነበረውን ነገርም አስተዋለ። ሆኖም እየመሸ ስለነበር ብዙ አልቆየም። ከአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርቱ ጋር ሌሊቱን በቢታኒያ አሳለፈ።

- በተከታዩ ቀን ወደኢየሩሳሌም ተመለሰ። ወደ ቤተ መቅደስም ገባ። በዚህ ጊዜ ግን እርምጃ ወሰደ። ሰዎች በቤተ መቅደሱ ውስጥ የተከለከለውን ነገር ያደርጉ ነበር። ለመስዋዕት የሚሆኑ እንስሳትን ይሸጡ ነበር። ኢየሱስ ሰዎቹ እያደረጉ የነበረው ነገር ትክክል አለመሆኑን ስለሚያውቅ ተገቢውን ነገር አደረገ። መግረፊያ ወይንም አለንጋ ከገመድ ጉንጉን አበጀ። ከዚያም ገንዘብ የሚለውጡትን ሰዎች በዚያ ከነበሩት በጎች፣ በሬዎችና እርግቦች ጋር በአንድ ላይ አባረራቸው። ገንዘብ የሚያስቀምጡበትን ጠረጴዛ ሲገለበጥም በላዩ ላይ የነበረው ገንዘብ በሙሉ በወለሉ ላይ ተበታተነ።

- እንዲህም አላቸው "እነኝህን ነገሮች ከዚህ አስወጧቸው፤ ቤቴ የፀሎት ቤት ትባላለች፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች መደበቂያ አደረጋችኋት።'

- የአይሁድ መንፈሳዊ መሪዎች በዚህ ሁሉ ስላልተደሰቱ ኢየሱስን የሚያጠፉበትን መንገድ ይፈልጉ ነበር። ሆኖም ሕዝቡ በኢየሱስ ትምህርት በጣም ደስተኞች ስለነበሩ በእርሱ ላይ እርምጃ ለመውሰድ አልደፈሩም።

- ኢየሱስ ክርስቶስ በመቅደስ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ አይነ ስውሮችና አንካሶች ወደእርሱ ይመጡና ይፈውሳቸው ነበር። ሕፃናትም "ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ ይሁን!" እያሉ ይጮኹ ነበር። የአይሁድ የኃይማኖት መሪዎች ይህን ሲሰሙ " ምን እያሉ እንደሚጮኹ ትሰማለህ ወይ?" ብለው ኢየሱስን ጠየቁት።

- በእርግጥም ኢየሱስ ምስጋናቸውን ሰምቶ ተቀብሎታል። ስለዚህም ለመሪዎቹ መልሶ "ይህ ምስጋና እውነተኛና ከልብ የፈለቀ የሕፃናት ምስጋና ነው።" አላቸው።

  *ይህ ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን ሲያነፃ የሚገልፀው ታሪክ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 21፡12 – 17 ይገኛል።*

http://gardenofpraise.com